<u>ለባለፈው ትምህርት ማሰሪያ</u>
ባለፉት ጥቂት የአገልግሎት ዓመታት ያየሁት ነገር ሁልጊዜ በአድማጭ missheared or misunderstood የመደረግ አደጋ (risk) አለ። ሆኖም ይህ ሁኔታ ሃላፊነት ለጎደለው ንግግርም ሆነ አቀራረብ ምክንያት መስጠት የለበት። ለምሳሌ:
- ነጻነት በተሰበከ ጊዜ ሁሉ ስድ የመለቀቅ አደጋ አለ:: ነገር ግን "ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም" እንዲሉ እውነቱን ከመናገር ዝም ማለትም አማራጭ ሊሆን አይችልም:: ይልቁን አስሮና አስገድዶ ሳይሆን በፈቃዳችን እንድናመልከው በሚወድ አምላክ እውነቱን ማወቅ የነጻነት መንገድ ብቻ ሳይሆን ወደ ሙላቱ የመድረስ / የmaturity ብቸኛ አማራጭ ነው::

*ኤፌ 5:17 ...ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ።*

*ሮሜ 12:2 የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ (በአእምሮአችሁ / mind) መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።*

- መጽሐፍ ቅዱሳችን የሚያስተምረው እንደአማኞች ለግል ሕይወታችን ያለውን የእ/ር ፈቃድ እንድናውቅ የተሰጠን ዋንኛ መንገድ በአእምሮ መታደስ መለወጥ ነው እንጂ ብዙ ጊዜ እንደምናሰበው ድንገት በሌላ ሰው ባላሰብነው መንገድና ሁኔታ ሲመጣ/ ሲነገረን የምናውቀው ነገር እንደሆነና ይህንን ናፋቂ እንድንሆን አይደለም።
- ይህን እንደ እንደተገለጠ የቃሉ ህግ እንላለን እንጂ እ/ር ለመንገዱ ፍሊጋ የለውም ተብሏልና በሚወደው መንገድ ሊናገረን እንደሚችልም መዘንጋት የለብንም::

# <u>ክፍል 4 - *ፈቃድ ሥልጣንና ፈቃድን መጫን* /manipulation/</u>

***<u>መግቢያ</u>***
ለሰው ስለተሰጠው ነጻ ፈቃድ መነጋገር ያለብን:
- በግላችን በሕብረታችንና በምንኖርበት ዓለም በሚሆነው ነገር የፈቃድ (የሰው፣ የእ/ር፣ እንዲሁም የጨለማው...) ድርሻ ምን እንደሆነ እንድናውቅና ያለንን ብዥታ ለማጥራት
- በእ/ር ፈቃድና በራሳችን ፈቃድ መሃል ያለውን ሕብረትና ልዩነት እንድናውቅ
- ከነጻ ፈቃድ ጋር አብሮ የተሰጠንን ሃላፊነት እንድናውቅና
- ነጻ ፈቃድን በአግባብ ያለማስተዳደርን (abuse የማድረግን) አደገኛነት እንድናውቅ

> *ዮሐ 8:32፣36 እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው።... እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ።*

ጠቃሚ መርሆዎች:
- ነጻነት ያለሃላፊነት ልቅነት (ስድነት) ነው!
- ነጻ ምርጫ በረከት የሆነውን ያህል ትልቅ ሸክም ነው!
- እያንዳንዳችን በአብዛኛው የምርጫዎቻችን ድምር ውጤት ነን! ብንወድም ባንወድም በየእለቱ የምንወስደው ምርጫና ውሳኔ ነገ ለምንሆነው ሰው የራሱን ድርሻ ያዋጣል:: ብዙ ጊዜ አማኞች በአፋችን ድንገተኛ ነገር እንደሌል ብንልም እንኳን በምግባራችን ግን ሁሉ ነገር በዛች ሚስጥራዊ በሆነች አንድ ቀን ድንገት (እኛ ሳናስበው) ይሆናል ብለን በምንጠብቀው ነገር ሕይወታችንን መሥርተን እንታያለን:: / "የአንድ ቀን ቲኦሎጂ"
- በአንዳንድ ሁኔታ ውስጥ ሃላፊነትን/ ተጠያቂነትን ፍራቻ ወይንም በሌላ ምክንያት በጊዜው አለመምረጥም ራሱ ምርጫ ነው! (የሮናልድ ሬገን ጫማ ምሳሌ)

> *ሐዋ 11:23 እርሱም መጥቶ የእግዚአብሔርን ጸጋ ባየ ጊዜ ደስ አለው፥ ሁሉንም በልባቸው ፈቃድ በጌታ ጸንተው ይኖሩ ዘንድ መከራቸው፤*

***<u>ፈቃድና ሥልጣን</u>***

*ዮሐ 10:18 እኔ <u>በፈቃዴ</u> አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት <u>ሥልጣን</u> አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ <u>ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ</u>።*

*ሐዋ 5:3-4 ጴጥሮስም፦ ሐናንያ ሆይ፥ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለ ምን ሞላ? ሳትሸጠው <u>የአንተ</u> አልነበረምን? ከሸጥኸውስ በኋላ <u>በሥልጣንህ</u> አልነበረምን? ይህን ነገር ስለ ምን በልብህ አሰብህ? እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም አለው።*

## ፈቃድን በአግባብ አለማስተዳደር - ፈቃድን መጫን / Manipulation

### Manipulation - ምን ማለታችን ነው?

- መገለልን ከመፍራት ወይንም ተቀባይነትን ላለማጣት የብዙሃኑን መንገድ ስንከተል፣ ከተጽእኖ የተነሳ ባሕላቸውን፣ ድርጊታቸውን መገለልን ከመፍራት ወይንም ተቀባይነትን ላለማጣት የብዙሃኑን መንገድ ስንከተል፣ ወይንም ባሕላቸውን፣ ሥርዓቶቻቸው ወይንም ድርጊታቸው ስንጋራ በmanipulation ሥር ነው ያለነው!
- ሁኔታዎችን ተጠቅመን ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ያለአግባብ የሌሎችን ፈቃድ በመጫን ከሚፈልጉት ውጪ እንዲያደርጉ አሉታዊ ተጽእኖ ማድረግ ወይንም ሌሎች በዚሁ መንገድ አሉታዊ ተጽእኖ እንዲያደርጉብን መፍቀድ ነው!
- ያለሥልጣናችን/ ከተሰጠን ሥልጣን አልፈን ፈቃድን መለማመድ ወይንም መፈጸም ነው!
- በተለይም የሌሎችን ፈቃድ ለራስ ጥቅም (advantage) ወይንም አላማ መጫን/ ወይንም መጠምዘዝ ነው! ስለዚህም ሥሩ ራስን ከፍ ከፍ የማድረግ (self-gratification) ፍላጎት ነው።
- አይነተኛ የልጅ ባሕሪይ ነው!
- በውድቀት ሌላውንም ይዞ የመውረድ ዝንባሌ ነው!
- የሌላውን ቀና ፍርድና ሚዛን የሚያጠፋ ፈቃድን በአግባብ የመምራት ጠላት ነው!
- ሰው የተፈጠረበትን መሠረታዊ ምክንያትና ሥርዓቱን የሚጻረር ነገር ነው!
- ለክርስቶስ ነጠላ (single) እና ሙሉ(whole) እንዳንሆን እንቅፋት የሚሆን የሰይጣንና የሥጋ ክንድ ነው!

### መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች:-

1. ካህኑ አሮን

*ዘጸ 32:1-*
*1: ሕዝቡም ሙሴ ከተራራው ሳይወርድ እንደ ዘገየ ባዩ ጊዜ፥ ወደ አሮን ተሰብስበው። ይህ ከግብፅ ምድር ያወጣን ሰው ሙሴ ምን እንደ ሆነ አናውቅምና ተነሥተህ በፊታችን የሚሄዱ አማልክት ሥራልን አሉት።*
*21-26: ሙሴም አሮንን፦ ይህን ታላቅ ኃጢአት ታመጣበት ዘንድ ይህ ሕዝብ ምን አደረገህ? አለው። አሮንም እንዲህ አለ፦ ጌታዬ ሆይ፥ ቍጣህ አይቃጠል ይህ ሕዝብ ክፋትን እንዲወድድ አንተ ታውቃለህ። እርሱም፦ ይህ ከግብፅ ምድር ያወጣን ሰው ሙሴ ምን እንደ ሆነ አናውቅምና በፊታችን የሚሄዱ አማልክት ሥራልን አሉኝ። እኔም። ከእናንተ ወርቅ ያለው ሰው ከእርሱ ሰብሮ ያምጣልኝ አልኋቸው ሰጡኝም በእሳትም ላይ ጣልሁት፥ ይህም ጥጃ ወጣ። ሙሴም በጠላቶቻቸው ፊት እንዲነወሩ አሮን ስድ ለቅቋቸዋልና ሕዝቡ ስድ እንደ ተለቀቁ ባየ ጊዜ፥ በሰፈሩ ደጅ ቆሞ። የእግዚአብሔር ወገን የሆነ ወደ እኔ ይምጣ! አለ የሌዊም ልጆች ሁሉ ወደ እርሱ ተሰበሰቡ።*
*…35 አሮን የሠራውን ጥጃ ስለ ሠሩ እግዚአብሔር ሕዝቡን ቀሠፈ።*

2. ንጉሥ ሳኦል

*መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 15: 23-24*
*ዓመፀኝነት እንደ ምዋርተኛ ኃጢአት፥ እልከኝነትም ጣዖትንና ተራፊምን እንደ ማምለክ ነው የእግዚአብሔርን ቃል ንቀሃልና እግዚአብሔር ንጉሥ እንዳትሆን ናቀህ አለ። ሳኦልም ሳሙኤልን፦ ሕዝቡን ስለ ፈራሁ፥ ቃላቸውንም ስለ ሰማሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝና የአንተን ቃል በመተላለፍ በድያለሁ።*

3. ንጉሡ አክዓብና ሚስቱ ኤልዛቤል

*መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 16:30-31*
*የዘንበሪም ልጅ አክዓብ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁሉ ይልቅ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ። በናባጥም ልጅ በኢዮርብዓም ኃጢአት መሄድ ታናሽ ነገር መሰለው፥ የሲዶናውያንንም ንጉሥ የኤትበኣልን ልጅ ኤልዛቤልን አገባ፥ ሄዶም በኣልን አመለከ ሰገደለትም።*

*መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 19:1-4*
*አክዓብም ኤልያስ ይህን ሁሉ እንዳደረገ፥ ነቢያትንም ሁሉ በሰይፍ እንደ ገደለ ለኤልዛቤል ነገራት። ኤልዛቤልም። ነገ በዚህ ጊዜ ነፍስህን ከእነዚህ እንደ አንዲቱ ነፍስ ባላደርጋት፥ አማልክት ይህን ያድርጉብኝ ይህንም ይጨምሩብኝ ብላ ወደ ኤልያስ መልእክተኛ ላከች። ኤልያስም ፈርቶ ተነሣ፥*

*ነፍሱንም ሊያድን ሄደ፥ በይሁዳም ወዳለው ወደ ቤርሳቤህ መጥቶ ብላቴናውን በዚያ ተወ። እርሱም አንድ ቀን የሚያህል መንገድ በምድረ በዳ ሄደ መጥቶም ከክትክታ ዛፍ በታች ተቀመጠና። ይበቃኛል አሁንም፥ አቤቱ፥ እኔ ከአባቶቼ አልበልጥምና <u>ነፍሴን ውሰድ ብሎ እንዲሞት ለመነ።</u>*

*መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 20:5-8*
*ሚስቱም ኤልዛቤል ወደ እርሱ መጥታ። ልብህ የሚያዝን እንጀራስ የማትበላ ስለምንድር ነው? አለችው። እርሱም፦ ኢይዝራኤላዊውን ናቡቴን፦ የወይንህን ቦታ በገንዘብ ስጠኝ ወይም ብትወድድ በፋንታው ሌላ የወይን ቦታ እሰጥሃለሁ ብዬ ተናገርሁት እርሱ ግን፦ የወይን ቦታዬን አልሰጥህም ብሎ ስለ መለሰልኝ ነው አላት። ሚስቱም ኤልዛቤል። <u>አንተ አሁን የእስራኤልን መንግሥት ትገዛለህን?</u> ተነሣ እንጀራም ብላ፥ ልብህም ደስ ይበላት የኢይዝራኤላዊውን የናቡቴን የወይን ቦታ እሰጥሃለሁ አለችው። በአክዓብም ስም ደብዳቤ ጻፈች፥ በማኅተሙም አተመችው በከተማው ወደ ነበሩትና ከናቡቴም ጋር ወደ ተቀመጡት ሽማግሌዎችና ከበርቴዎች ደብዳቤውን ላከች።....*

*15 ኤልዛቤልም ናቡቴ ተወግሮ እንደ ሞተ በሰማች ጊዜ ኤልዛቤል አክዓብን፦ ናቡቴ ሞቶአል እንጂ በሕይወት አይደለምና በገንዘብ ይሰጥህ ዘንድ እንቢ ያለውን የኢይዝራኤላዊውን የናቡቴን የወይን ቦታ ተነሥተህ ውረስ አለችው።*
*<u>በእግዚአብሔር ፊት ክፋት ለመሥራት ራሱን እንደ ሸጠ፥ ሚስቱም ኤልዛቤል እንደ ነዳችው፥ እንደ አክዓብ ያለ ሰው አልነበረም። ...</u>*
*27-29 አክዓብም ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ልብሱን ቀድዶ ገላውን ማቅ አለበሰ፥ ጾመም፥ በማቅ ላይም ተኛ፥ ቅስስ ብሎም ሄደ። ደግሞም፦ አክዓብ በፊቴ እንደ ተዋረደ አየህን? በፊቴ የተዋረደ ስለ ሆነ በልጁ ዘመን በቤቱ ላይ ክፉ ነገር አመጣለሁ እንጂ በእርሱ ዘመን ክፉ ነገር አላመጣም የሚል የእግዚአብሔር ቃል ወደ ቴስብያዊው ወደ ኤልያስ መጣ።*

*[ራዕ 2:20 ዳሩ ግን። ነቢይ ነኝ የምትለውን ባሪያዎቼንም እንዲሴስኑና ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉ የምታስተምረውንና የምታስተውን ያችን ሴት ኤልዛቤልን ስለምትተዋት የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤]*

- እውነተኛ ሴት ነበረች የሚሉ አሉ…
- ሌላም ትሁን የእውነተኛዋ ኤልዛቤል ምሳሌ በባሕሪዋና በግብሯ እንደመጀመሪያዋ ኤልዛቤል ሌሎችን ለእግዚአብሔር እንዳይገዙ በትንቢቷና በትምህርቷ ወደ እርሷ ርኩሰት የምትጎትት ነበረች።

<u>*ፈቃድን የመጠምዘዝ/ የመጫን (የManipulation) መሣሪያዎች*</u>

1. **ፍርሃት**

- **በሌሎች መጠላት ወይንም መገለል**/ Rejection በመፍራት ሰዎች የማይፈልጉትን ወይንም የማይገባቸውን ሲያደርጉ ለManipulate ተዳርገዋል:: ይሄ በተለይ በታዳጊ ወጣቶች መሃል በጣም የተለመደና ብዙ ወጣቶችን እስረኛ የሚያደርግ ነገር ነው:: ብዙዎችም ከዚህ የተነሳ ሳያስቡት ለሱስ ይዳረጋሉ::
- **ቅጣትን** በመፍራት ሰዎች የማይፈልጉትን ወይንም የማይገባቸውን ሲያደርጉ ለManipulate ተዳርገዋል::
    - ለምሳሌ በትዳር ውስጥ ግንኙነትን በመከልከል የባልን ወይንም የሚስትን ፈቃድ ለማሸነፍ መሞከር የmanipulation አሰራር ነው::
    - ልጆች ከፍርሃት የተነሳ ሳይሆን በፍቅር መታዘዝን መማር አለባቸው:: የአባትነት/ የወላጅነት ምሳሌያችን እ/ርም እንድንታዘዘው የሚፈልገው በፍርሃት ሳይሆን በፍቅር ነው!

        "ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ!"

        የትእዛዛት ሁሉ መጀመሪያ…

2. **የኩነኔ ወይንም የጥፋተኝነት ስሜት** / Guilt

- የኩነኔ ስሜት ሰው ራሱን ያለአግባብ እንዲቀጣ/ ወይንም እንዲጨቁን ያደርገዋል፤ ከራሱም አልፎ ሌላውን አለአግባብ የሚኮንን ይሆናል፤ በሥራ ለመጽደቅ የመፈለግ ዝንባሌም አብሮ የሚዳብር ነገር ነው።

- አንድ ሰው በአንድ ጉዳይ ራሱን ጥፋተኛ አድርጎ ከተቀበለ ከዚያ በኋላ (naturally) የሚያደርገው ነገር ከሀሊናው ክስ ለመዳን ወይንም ለጥፋቱ ካሳ ለማቅረብ ሲል ራሱን ያለአግባብ አሳልፎ ይሰጣል::
- ሰዎች ራሳቸውን እንዲሰጡ /በሃይማኖታቸው committed እንዲሆኑ/ ብዙ ሃይማኖቶች የሚጠቀሙበት መሳሪያ ይኸው የኩነኔ ስሜት ነው::

3. አግባብ የሌለው ርህራሄ/ Sympathy
- ብዙውን ጊዜ በልቅሶ ወይንም በኩርፊያ ወይንም በሚያሳዝን ንግግር የሌሎችን ልብ ለማሸነፍ ስንሞክር ወይንም ከዚህ የተነሳ ያለአግባብ ለሌሎች ስንራራ በmanipulation አሰራር ተጽእኖ ውስጥ ነን::
    - ለምሳሌ ልጆች ልቅሶን በዚህ መንገድ ሊፈቀድላቸው የማይገባውን ነገር እንዲፈቀድላቸው ያለአግባብ ስሜታችንን ለመጫን ሲሞክሩ

<u>የManipulation አሠራር አይነተኛ መገለጫ ሥፍራዎች</u>

1. በቤተሰብ ውስጥ
ዋንኛው የመገለጫው ቦታ ነው!

**ልጆች በወላጆቻቸው ላይ**
- ሊፈቀድላቸው የማይገባውን ነገር እንዲፈቀድላቸው ያለአግባብ ስሜታችንን ለመጫን ሲሞክሩ
- "አትወጂኝም/ አትወደኝም፣ ብትወደኝ/ጅኝ...(ይህና ያንን ታደርግልኝ ነበር)" በማለት
- በልቅሶና ኩርፊያ...

ካህኑ ኤሊ ልጆቹን ሊቀጣ ባለመቻሉ... / 1ሳሙ 2:22-

**ወላጆች በልጆቻቸው ላይ**
ልጆችንን እርሱ ሊሆን እንደሚገባው ሳይሆን እኛ እንደምንፈልገው እንዲሆንልን ካለን ፍላጎት ይጀምራል። እኛ ልንመርጥለት ልንወስንለት ልናስገድደው፣ ስንችል በሃይል ሳንችል በጥቅም (አንዳንዴም በውሸት ተስፋ) ወይንም በቀጣት ፈቃዱን ልንቀይር/ እኛ የፈለግነውን ልናስደርገው ስንሞክር... ማለት ነው። ልሂ ችግር ደግሞ የሕይወቱን ትልልቅ ምርጫዎች / ጋብቻን ሳይቀር/ ለመወሰን እስከመሞከር በኋላም አግብቶ/ታም ጣልቃ እስከ መግባት ይዘልቃል።
በዚህም የእ/ር መሠረታዊ ዓላማ እንጻረራለን።

*ምሳ 22:6 ልጅን <u>በሚሄድበት</u> መንገድ ምራው፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።*
*ዘፍ 2:24 ስለዚህ ሰው <u>አባቱንና እናቱን ይተዋል</u>፥ በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።*

**ሚስት በባሏ ላይ**
- የኤልዛቤል ምሳሌነት
- በተለይም ተፈጥሮአዊ ፍላጎቱ በሆኑት ነገሮች
    - ...ግንኙነት በመካልከል
      *(1ቆሮ 7:4-5 ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፥... ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፥ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ።)*
    - በቃላት ሞራሉን በሚነካ ንግግር / በማንቋሸሽ / በተለይ በአደባባይ
    - ለማስቀናት በመሞከር
- እነዚህን ነገሮች ለማግኘት ሲል ያለአግባብ የእርሷ ተገዢ ሲሆን

**ባል በሚስቱ ላይ**
- ከባሏ በጣም በምትፈልጋቸው ነገሮች
    - ፍቅርን ሆን ብሎ በመሰወር / በአጉል ኩራት
    - በፈለገችው ጊዜ ባለመገኘት / ራስን በማዋደድ
    - ....
- እነዚህን ነገሮች ለማግኘት ስትል ያለአግባብ የእርሱ ተገዢ ስትሆን

**በእጮኝነት ግንኙነት ውስጥ**
- "አትወጂኝም/ አትወደኝም፤ ብትወደኝ/ጅኝ..." / ብዙ ወጣቶች ድንግልናቸውን ከጋብቻ በፊት እንዲያጡ ከሆኑበት መንገድ አንዱ ነው
- "ብትተወኝ... etc. ራሴን አጠፋለሁ ወይንም (እንዲህና እንዲያ) አደርጋለሁ"
- "ያለአንተ/ያለአንቺ መኖር አልችልም"

2. **በቤ/ክ በተለይ በአመራር አካባቢ**
- ሕዝብ በመሪዎች ላይ - በdemocracy መንፈስ አሰራር ወደ እግዚአብሔር ሃሳብ ሳይሆን ወደ ሕዝቡ ሃሳብ እንዲያዘነብሉ ጫና በማድረግ፣ ይህም በአቋማቸው ላይ እንዲያመቻምቹ (compromise እንዲያደርጉ) ተጽእኖ ያደርጋል:: ይህ ችግር በተለይ በሕዝብ ምርጫ በተሰየሙ የቤ/ክ መሪዎች በምትመራ ቤ/ክ የተለመደ ነው::
- በሕዝብ ተሰሚነት ወይንም ተወዳጅነት ያለው አገልጋይ የመሪዎችንም ሆነ የሕዝብን ፈቃድ የሚጫን ነገር በማድረግ manipulative ሊሆን ይችላል:: ብዙ ጊዜ ቤ/ክንን የሚከፍሉ ሰዎች በዚህ አሰራር ተጽእኖ ውስጥ ያሉ ናቸው!
- ብዙ ገንዘብ ሰጪ የሆነ ሰው ወይንም በሌላ ምክንያት ብዙ ተፈላጊ የሆነ ሰው manipulative ሊሆን ይችላል::

3. **ከሰዎች ጋር ባለን ማንኛውም ግንኙነት ውስጥ**
    - በተለይ በታዳጊ ወጣቶች መሃል: pear-pressure - ሞራልን በሚነካ የሹፈት(mocking) ወይንም የማንቋሸሽ (intimidating) ንግግር ያልፈለጉትን ወደማድረግ እንዲገፋፉ፣ የሌላውን ባሕል እንዲቀበሉ ሲሆኑ፤
    - አዋቂዎችም ሆነን ከወዳጆቻችን፣ ከሥራ ባልደረባዎቻችን ጋር ባለን ግንኙነት፤
    - በሌሎችም ተመሳሳይ ግንኙነቶች ውስጥ ሁሉ ሊገለጥ የሚችል ነገር ነው
    - የተለመዱ manipulative ንግግሮች:- "ጣል ጣል አደረግኸኝ/ሽኝ" "...እንደምትፈልገ/ጊው አውቃለሁ"

በዚህ ዓይነት ተጽእኖ ውስጥ የሚኖር ሰው:
- በሕይወቱ፡ በአገልግሎቱ በቀላሉ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ያለመቻል ችግር ወይንም የማመቻመች ችግር ይገጥመዋል / ውሎ ሲያድርም ያለመጥቀም (worthlessness) ስሜት፣ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት፣ አልፎም ሃዘንና ኩነኔ ሊሰማው ይችላል
- የኩነኔ ስሜት ደግሞ ሰው ራሱን ያለአግባብ እንዲቀጣ/ ወይንም እንዲጨቁን ያደርገዋል፤
- ከራሱም አልፎ ሌላውን አለአግባብ የሚኮንን ይሆናል፤ በሥራ ለመጽደቅ የመፈለግ ዝንባሌም አብሮ የሚዳብር ነገር ነው።

ብዙውን ጊዜ manipulate ሲደረጉ የኖሩ ሰዎች ራሳቸው ደግሞ manipulative ይሆናሉ::
- ይህ ችግር የቆላስያስ ቅዱሳንም ይደርስባቸው ከነበረው ጫና ጋር እና የገላትያ ቅዱሳን ከወደቁበት አዚም ጋር በቀጥታ ይመሳሰላል። ስለዚህ መፍትሄውን በነዚህ መጽሐፍት ውስጥ በአጭሩ ማየት እንችላለን።

**መፍትሄው**

*ቆላስ 2:18-23 ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ እየወደደ፥ ባላየውም ያለ ፈቃድ እየገባ፥ በሥጋዊም አእምሮ በከንቱ እየታበየ ማንም አይፍረድባችሁ። እንደዚህ ያለ ሰው ራስ ወደሚሆነው አይጠጋም፥ ከእርሱም አካል ሁሉ በጅማትና በማሰሪያ ምግብን እየተቀበለ እየተጋጠመም፥ እግዚአብሔር በሚሰጠው ማደግ ያድጋል። ከዓለማዊ ከመጀመሪያ ትምህርት ርቃችሁ ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ፥ እንደ ሰው ሥርዓትና ትምህርት። አትያዝ፥ አትቅመስ፥ አትንካ ለሚሉት ትእዛዛት በዓለም እንደምትኖሩ ስለ ምን ትገዛላችሁ? እነዚህ ሁሉ በመደረግ ሊጠፉ ተወስነዋልና። ይህ እንደ ገዛ ፈቃድህ በማምለክና በትሕትና ሥጋንም በመጨቆን ጥበብ ያለው ይመስላል፥ ነገር ግን ሥጋ ያለ ልክ እንዳይጠግብ ለመከልከል ምንም አይጠቅምም።*

*ገላ 3:1 የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ፥ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው?*
*ገላ 5:1 በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ።*

## ክፉን የማሸነፍ አይነተኛ መንገድ!

Manipulation ሾላካ (subtle) አሰራር እንደመሆኑ ለmanipulation የመጀመሪያው ምላሻችን ሊሆን የሚገባው Manipulationን Manipulation ነው ብሎ ፊት ለፊት መቃወም ነው!

*ኤፌ 5:8-12 ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና፥ አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ፤ የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ፥ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ፤ ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፥ ይልቁን ግለጡት እንጂ፥ እነርሱ በስውር ስለሚያደርጉት መናገር እንኳ ነውር ነውና፤*

*2ቆሮ 2:11 በሰይጣን እንዳንታለል፤ የእርሱን አሳብ አንስተውምና።*

**ተጨማሪ ክፍሎች**

*ዕብ 9: 14 ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ሕሊናችሁን ያነጻ ይሆን?*

*ዕብ 10:19-22 እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን፥ በእግዚአብሔርም ቤት ላይ የሆነ ታላቅ ካህን ስላለን፥ ከክፉ ሕሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውኃ ታጥበን በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ፤*

ሮሜ 6:18, 22; 8:1 -- ከሃጢያትና ከኩነኔ ነጻ ወጥታችኋል!

ራዕ 12:10 የወንድሞች ከሳሽ ተጥሏል!

---

ከትምህርቱ ጋር በተያያዘ ጥያቄ ቢኖርዎት በሚከተለው አድራሻ ሊያገኙን ይችላሉ:-

**አልዓዛር**
ስልክ.ቁ. 0735964768 ወይንም
ኢ.ሜል alazar_1@yahoo.com